የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር ኀ/162/11/833

ቀን ታሕሣስ 25 2015 ዓ.ም

ለመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/

<u>አዲስ አበባ</u>

**ጉዳዩ፣ <u>የፓርቲውን ጠቅላላ ጉባዔ በድጋሚ እንዲደረግ ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ ስለማሳወቅ፤</u>**

ሚያዚያ 22 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር መኢአድ/049/2014 በተጻፈ ደብዳቤ ፓርቲው ሚያዚያ 9 ቀን 2014 ዓ.ም. ያካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ በሚመለከት ሪፖርት ማቅረባችሁ ይታወቃል።

ስለሆነም ቦርዱ ታህሳስ 19 ቀን 2015 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ ፓርቲው ከሪፖርቱ ጋር አያይዞ ያቀረባቸውን ሰነዶች ከሕጉ፣ ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ እና የቦርዱ ታዛቢዎች ካቀረቡት ሪፖርት አንፃር መርምሯል።

**ጠቅላላ ጉባዔውን በተመለከተ**

**ሀ)** በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ የተካሄደው የፓርቲው ፕሬዝዳንት ምርጫ በአዋጅ አንቀጽ 74(3) መሠረት በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ ሂደት የተከናወነ በመሆኑ ቦርዱ ተቀብሎ መዝግቧል።

**ለ)** በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ የተካሄደው የፓርቲው የኦዲት እና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ አባላት፤ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት እና የተጓደሉ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ምርጫ እጅ በማውጣት መደረጉ በአዋጅ አንቀጽ 74(3) መሠረት በየደረጃው ያሉ

ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ-ገጽ
www.nebe.org.et

አመራሮች አመራረጥ ግልጽ፣ ነጻ እና ፍትሃዊ እንዲሁም በሚስጥር በሚስጥ ድምጽ የሚመረጡ መሆን እንዳለበት ከሚደነግገው ጋር የተቃረነ በመሆኑ ፓርቲው ሕጉን መሠረት በማድረግ በድጋሚ ጠቅላላ ጉባኤ ሊያካሂድ እንደሚገባ ቦርዱ ወስኗል፡፡

**የመተዳደሪያ ደንቡን በተመለከተ**

**ሀ)** በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 18.1.6 ፕሬዝዳንቱ በጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣል፤ 18 የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በፕሬዝዳንቱ ተመርጠው በማዕከላዊ ም/ቤት አባላት ይጸድቃሉ፤ የሚለው ከአዋጁ አንቀጽ 74/3 እና ከተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 18.1.1 ጋር የሚቃረን በመሆኑ፤

**ለ)** በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 19.3 የፓርቲው አምስት ም/ፕሬዝዳንቶች በፕሬዝዳንቱ ተመርጠው፤ በጠቅላላ ጉባኤ ይጸድቃሉ፤ የሚለው ከአዋጁ አንቀጽ 74/3 እና ከተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 18.1.1 ጋር የሚቃረን በመሆኑ፤

**ሐ)** በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 13.1 የዞን ም/ቤት አባላት ብዛት በግልጽ በቁጥር ያልተቀመጠ በመሆኑ፤

**መ)** በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 18.5.1 መሰረት ጠቅላላ ጉባኤው ምልዓተ ጉባኤው የሚሟላው ከ 5% ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ውስጥ 500 ሲገኙ ይሆናል በማለት የተደነገገው ግልጽ ባለመሆኑ፤

ሠ) በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 74(1) (ኘ) መሰረት የፓርቲው የውስጥ አለመግባባቶች አፈታት ስርአት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ በሕጉ መሠረት በማካተት መቅረብ ያለበት በመሆኑ፤

በዚሁ መሠረት ፓርቲው በድጋሚ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያካሂድ እና ተሻሽሎ የቀረበው የፓርቲው መተዳዳሪያ ደንብም ከላይ ከተራ ቁጥር ከ **"ሀ"** - **"ሠ"** የተገለፁትን በሕጉ መሠረት በማካተት ሊያሻሽል እና በጠቅላላ ጉባኤው ሊያጸድቅ ይገባል፡፡

**በመሆኑም፡-**

1ኛ/ ፓርቲው ከዚህ በላይ የተገለጸውን ጉባኤ ጠርቶ እስከሚያጸድቅ ድረስ ከህጉ ጋር የሚቃረኑ የደንቡ አንቀጾች የታገዱና በአዋጅ 1162/2011 ላይ በዝርዝር የሰፈሩት በተግባር እንዲፈጸሙ እንዲደረግ፤

2ኛ/ ፓርቲው ይህ ውሳኔ ከተገለጸበት ከታህሳስ 25 ቀን 2015 ዓ.ም. ጀምሮ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ማለትም እስከ ሚያዚያ 25 ቀን 2015 ዓ.ም. ድረስ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያካሂድ፣

3ኛ/ በየደረጃው ያሉ የአመራር ምርጫን በሚመለከት ግልጽ፣ ነጻ እና ፍትሃዊ እንዲሁም በሚስጥር በሚሰጥ የድምፅ አሰጣጥ፣ የድምፅ ቆጠራ እና ፤ እንዲሁም ውጤት አገላለፅ በሕጉ መሠረት እንዲከናወኑ እንዲያደርግ፤

**4ኛ**/ ፓርቲው ከላይ ከተራ ቁጥር **"ሀ" - "ሠ"** የተገለፁትን የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፆች ላይ ማሻሻያ በማድረግ ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ በፊት ማሻሻያ የተደረገባቸው የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፆች የተካተቱበት ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብ ጉባኤው ከሚካሄድበት 5 የስራ ቀናት አስቀድሞ ለቦርዱ እንዲያቀርብ፣

**5ኛ**/ ከላይ የተገለፁት ማስተካከያዎች የተደረገበት እና በቦርዱ በቅድሚያ የታየ የተሻሻለ የመተዳደሪያ ደንብ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ በማስወሰን እንዲያቀርብ፤

**6ኛ**/ ፓርቲው የጉባኤው ዝርዝር ሂደት እና ውሳኔ የሚገልጽ ቃለ ጉባኤ፣ በጉባኤው የፀደቀውን መተዳደሪያ ደንብ እና የጠቅላላ ጉባኤውን ሪፖርት ጉባኤው በተካሄደ በ15 ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ ቦርዱ የወሰነ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምክትል ሰብሳቢ
Deputy Chairperson National Electoral Board